የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ
(……..2016 ዓ.ም እንደተሻሻለ)

መግቢያ

"የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር" ሲከራከርለት የነበረው ሙያውን የሚያስተዳድር የጠበቆች ማኅበር በሕግ የተቋቋመ በመሆኑ፣

በአንጻሩም ፈቃደኛ የሆኑ የሕግ ባለሞያዎችን በማስተባበር ለሕግ የበላይነትና ለፍትህ መስፈን፣ ለሥነ ሕግ እድገት እንዲሁም የሕግ ሙያ የላቀ ደረጃ እዲኖረው ለመርዳት፤ ለመልካም አስተዳደር መጎልበት ብሎም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መሥራት የማያቋርጥ ዓላማ መሆኑን በመገንዘብ፣

ማኅበሩ ለእነዚህ ዓላማዎች መሳካት መሥራት የሚያስችለው ሰፊ ሁኔታ ያለ በመሆኑ እና ይህም ከማንኛውም የሕግ ባለሙያ የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን በማመን፣ በተጨማሪም ማኅበሩ በራሱ ከሚያደርጋቸው ጥረቶች በተጓዳኝ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ለመሥራት የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ይረዳው ዘንድ መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በ2001 ዓ.ም የፀደቀው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁ 1113/2011 መሠረት እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

አንቀጽ 1
እንደገና ምዝገባና አስተዳደር

ማኅበሩ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁ 1113/2011 መሠረት እንደገና የተመዘገበና የሚተዳደር ነው፡፡

አንቀጽ 2
ስለማኅበሩ ስም

የማኅበሩ መጠሪያ "የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር"(Ethiopian Lawyers Association) ነው፡፡

አንቀጽ 3
ስለማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት

3.1 የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 13፣ የቤት ቁጥር 903/7 ነው፤

3.2 ማኅበሩ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ኮሚቴዎችን ወይም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ያደራጃል፤

3.3 የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ ሊቀየር ይችላል፡፡

አንቀጽ 4
ስለ ማኅበሩ አርማ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (Ethiopian Lawyers Association) የራሱ አርማ ይኖረዋል::

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 5
ስለማኅበሩ ዓላማዎች

ማኅበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

5.1. የሕግ የበላይነት እንዲሰፍንና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ፣

5.2. የፍትሕ አስተዳደር በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያስችሉ ጥናቶችን ማድረግና እና ሐሳብ መሥጠት፣

5.3. በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ላይ ጥናት በማድረግ፣ ችግሮች ሲታዩ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ የሕግ አስተያየቶችን ወይም የሕግ ረቂቆችን በማቅረብ የፍትሕ ስርዓቱ እንዲሻሻል ማገዝ፣

5.4. ሥነ-ሕግ እንዲያድግ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ፣

5.5. የሕግ ሙያ እንዲከበር እና የሕግ ባለሙያው መብት እንዲጠበቅ መሥራት፣

5.6. የፍትሕ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በራሳቸው ወጭ ጠበቃ ማቆም ለማይችሉ ሰዎች በነፃ የሕግ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

5.7. የማኅበሩ አባላት ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙና በመካከላቸውም የመቀራረብ፣ የመግባባትና የመተባበር መንፈስ እንዲሠፍን ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

5.8. የሕግ ባለሙያዎች በሕግ ጥናትና ምርምር ሥራዎች በስፋት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ይህንን ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል መጽሔት እና ሌሎችም ሕትመቶችን ማውጣት፣

5.9. የሕብረተሰቡን የሕግ ንቃተ ህሊና ለማሳደግና ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን እንዲያውቅና ግዴታውን እንዲወጣ መፅሔቶችን፣ ጋዜጦችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ ሴሜናሮችን እና ሌሎች መንገዶች በመጠቀም ማስተማር፣

5.10. የሕግ ሙያ እንዲከበር የሚያስችሉ ሥራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር መሥራት፣

5.11. የሕግ እውቀትን ለማሳደግ ከሕግ ተቋሞችና ከተመሳሳይ ማኅበሮች ጋር በመተባበር የሙያ ማሻሻያ ኮርሶችን፣ ሥልጠናዎችን እና ትምህርታዊ ውይይቶችን ማዘጋጀት፤

5.12. በሕግ ሙያ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ባለሞያዎች እውቅና መስጠት::

5.13. የተለያዩ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በሥራ ላይ በሥፋት እንዲውሉ በመደገፍ እና በመሥራት ግጭቶች እና አለመግባባቶች እንዲቀንሱ መርዳት::

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 6
ስለማኅበሩ ተግባር

ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ይሠራል።

አንቀጽ 7
ሰለ አባልነት

7.1 ማኅበሩ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የአባልነት መስፈርቱን አሟልተው፣ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ አባል የሆኑና የአባልነት መዋጮ ለመክፈል እና ግዴታቸውን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆኑ አባላትና ተባባሪ አባላት ይኖሩታል፣

7.2 ማንኛውም እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የተመረቀ የሕግ ባለሙያ የማኅበሩ አባል መሆን ይችላል፣

7.3 ማንኛውም እውቅና ባለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሕግ ተማሪ የሆነ ወይም የሕግ ባለሙያ ባይሆንም የማኅበሩን ዓላማዎች የሚደግፍ ማንኛውም ሰው የማኅበሩ ተባባሪ አባል መሆን ይችላል፣

7.4 ማኅበሩ ከአባላትና ከተባባሪ አባላት በተጨማሪ የክብር አባላት ይኖሩታል።

7.5 የክብር አባላት የሕግ ባለሙያ ባይሆኑም የማኅበሩን ዓላማዎች በመደገፍ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉ እና የክብር ዓባልነት ጥያቄ ያቀረቡ ወይም ማኅበሩ የክብር ዓባል እንዲሆኑ የሚጋብዛቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ናቸው።

7.6 ማኅበሩን በተለያየ መንገድ ሲያገለግሉ የነበሩ ባለሙያዎች፤ የማኅበሩን ዓላማ የሚደግፉ ተቋማትና የጥብቅና ድርጅቶች እንዲሁም ከፍተኛ አስተዕኦ ያበረከቱ አካላት የማኅበሩ የክብር አባላት እንዲሆኑ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊወሰን ይችላል።

7.7 የክብር አባልነት የሚከናወንበትን ዝርዝር ሁኔታ በተመለከተ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ዝርዝር ያፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

7.8 ማንኛውም ግለሰብ የማኅበሩ አባል፣ የክብር አባል ወይም ተባባሪ አባል መሆን የሚችለው አባልነቱ፣ የክብር አባልነቱ ወይም ተባባሪ አባልነቱ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፀድቅ ብቻ ነው።

አንቀጽ 8
ሰለአባላት እኩልነትና መብቶች

8.1 የማኅበሩ አባላት ሁሉ አንድና እኩል የሆነ ድምፅ አላቸው፣

8.2 የማኅበሩ አባላት የመምረጥ፣ የመመረጥና በማናቸውም ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስንባቸው ጉዳዮች በራሳቸው ወይም በወኪላቸው አማካይነት ድምፅ የመስጠት መብት አላቸው።

8.3 የማኅበሩ የክብር አባላት እና ተባባሪ አባላት ከመምረጥ፣ ከመመረጥ እና ለውሳኔ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ድምጽ ከመስጠት በስተቀር አባላት ያሏቸው ሌሎች መብቶች ሁሉ ይኖሯቸዋል፣

8.4 ከላይ በተ.ቁ. 8.3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ስለ አባላት የሚደነግጉት የዚህ ደንብ አንቀጾች በተባባሪ አባላት እና የክብር አባላት ላይም ተፈፃሚ ናቸው።

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

8.5 አባላት፣ ተባባሪ አባላት እና የክብር አባላት በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የመሳፈልና አስተያየት የመስጠት፣ ስለማኅበሩ መረጃ ጠይቆ የማግኘትና ማኅበሩ በሚያበረክታቸው አገልግሎቶች የመጠቀም፣ አባላት በቃለ-ጉባዔ ልዩነታቸውን የማስመዝገብ መብት አላቸው።

8.6 በዚህ ደንብ መሠረት አባሉንና ተባባሪ አባሉን በተመለከተ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚተላለፉበት የዲስፕሊን ወይም ሌሎች ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ አባልና ተባባሪ አባል ለጠቅላላ ጉባዔው ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።

8.7 በአንቀጽ 9.6 መሠረት አንድ አባል የሚጠበቅበትን የአባልነት መዋጮ ካልከፈለ በአባልነት መብቱ አይሠራበትም።

አንቀጽ 9
ስለአባላት ግዴታዎች

ማንኛውምም አባል፡-

9.1 ማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ የማክበር፣
9.2 በጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነውን የአባልነት ክፍያና መዋጮ የመክፈል፣
9.3 ማኅበሩ የሚሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ተቀብሎ የመወጣት፣
9.4 ለሕግ የበላይነት፣ ለፍትሕ መስፈን መቆም፣ የሕግ ሙያን ሥነ ምግባርና ሙያው የሚጥልበትን ኃላፊነት የመጠበቅና የማክበር፣
9.5 የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች የማክበር ግዴታ አለበት።
9.6 ማንኛውም አባል በመምረጥ፣ በመመረጥ እና ድምጽ በመስጠት መብቱ መጠቀም የሚችለው ያለበት ውዝፍ የአባልነት መዋጮ ከሶስት ወር ያልበለጠ ከሆነ ብቻ ነው።

አንቀጽ 10
አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

10.1 አባልነት ወይም ተባባሪ አባልነት ወዲያው የሚቋረጠው አባሉ፣
10.1.1 ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፤
10.1.2 ከአባልነት መልቀቁን በጽሁፍ ሲያሳውቅ፤
10.1.3 ከአንድ ዓመት በላይ የመዋጮ ውዝፍ ሲኖርበትና ማስጠንቀቂያ በፁሑፍ በደረሠው በ15 ቀን ውስጥ ውዝፉን ሳይከፍል ከቀረ ይሆናል።

10.2 ማንኛውም አባል የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ ከተላለፈ፣ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያወጣውን በአባል ላይ የሚፈጸሙ መመሪያዎችን ከጣሠ ወይም የሚሰጡትን ኃላፊነቶች ባለማባቡ ካልተወጣ፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ከአባልነት ሊያግደው ወይም ሊሰርዘው ይችላል። ዝርዝር አሠራሩም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፣

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ11
ስለማኅበሩ አወቃቀርና አመራር

11.1 ማኅበሩ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡

11.1.1 ጠቅላላ ጉባዔ፣

11.1.2 ኦዲተር፣

11.1.3 የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ፣

11.1.4 ልዩ ልዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች፣

11.1.5 ዋና ዳይሬክተር፣

11.2 የማኅበሩ መዋቅር የሚከተለው ይሆናል፡-



DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 12
ስለጠቅላላ ጉባዔው ሥልጣን

12.1 ጠቅላላ ጉባዔው የማኅበሩ ከፍተኛው የአመራር አካል ነው።

12.2 ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፣

12.2.1 የማኅበሩን ስትራቴጂክ ፕላን፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣

12.2.2 በሚቀርቡለት ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የኦዲት ሪፖርቶች እንዲሁም በሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፤

12.2.3 የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ እንዲሁም በአባላት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መመሪያዎችን ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፣

12.2.4 የማኅበሩን ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና ፀሐፊ፣ ሂሳብ ሹም እና ሌሎች ሦስት (3) የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤

12.2.5 የማኅበሩን ኦዲተር ይሾማል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤

12.2.6 ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ያልቻሉ የማኅበሩን ተመራጮች ከኃላፊነት ያሰናብታል፤

12.2.7 የማኅበሩን የአባልነት ክፍያና ሌሎች መዋጮዎችን ይወስናል፤

12.2.8 አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያወጣቸውን የማኅበሩን የውስጥ መመሪያዎች ያሻሽላል፤

12.2.9 ከአባልነት በመሠረዝ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ እንዲሁም

12.2.10 በማኅበሩ መፍረስ ላይ ይወስናል።

አንቀጽ 13
ስለጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች

13.1 ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይኖሩታል::

13.2 የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል፤

13.3 የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ። ድምፅ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

13.4 የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ አጀንዳ

13.4.1 የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱን እና የኦዲተሩን ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥ፤

13.4.2 በደንቡ የተወሰነው የሥራ ጊዜ ሲያበቃ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላትን መምረጥ፣ የውስጥ ኦዲተሩን መሰየም፤

13.4.3 ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ማየት፣ መወሰን፣

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

13.5 የመደበኛ ስብሰባ ማስታወቂያ

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት በሥራ አስፈፃሚው ቦርዱ መመሪያ መሠረት ተገቢ ነው ብሎ በሚያምንበት ዘዴ ቢያንስ የ7 ቀን ማስታወቂያ በመስጠት ስብሰባውን ይጠራል፡፡ ማስታወቂያውም የስብሰባውን ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ ይገልፃል፡፡

13.6 ምልዐተ ጉባዔ

13.6.1 በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9.6 የተጠቀሰውን ግዴታ ከፈፀሙ አባላት አምሳ በመቶ (50%) በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል፡፡

13.6.2 ከደንብ ማሻሻል በቀር በንዑስ ቁጥር 13.6.1 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባዔው ካልተሟላ ለሦስተኛ ጊዜ በሚጠራ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በተገኙት አባላት ብቻ ምልዓተ ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡ ሁለተኛው ጉባዔ የመጀመሪያ ጉባዔው በተጠራ በ15 ቀን ውስጥ፣ ሦስተኛው ጉባዔ ሁለተኛው ጉባዔ በተጠራ 15 ቀን ውስጥ መጠራት አለበት፡፡

13.7 አስቸኳይ ስብሰባ ስለመጥራት፣

13.7.1 ማናቸውም ከመደበኛው ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ውጪ የሚጠራ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ አስቸኳይ ስብሰባ ይሆናል፡፡

13.7.2 አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን ያላቸው፣

13.7.2.1 የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ በሁለት ሦስተኛ ($^2/_3$ኛ) ድምጽ፣

13.7.2.2 ከማኅበሩ ጠቅላላ አባላት አስር በመቶ (10%) በላይ የሆኑና በአንቀጽ 9.6 መሠረት ከሦስት ወር በላይ ውዝፍ የአባልነት መዋጮ የሌለባቸው አባላት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራላቸው በፊርማ የተደገፈ ማመልከቻ ሲያቀርቡ፣

13.7.2.3 የማኅበሩ የውስጥ ኦዲተር በማኅበሩ የሥራ አፈፃፀም ላይ ከባድ ጉድለት አግኝተው አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ፣

13.8 የስብሰባው አጠራር

በንዑስ አንቀጽ 13.7 መሠረት የአስቸኳይ ሰብሰባ እንዲደረግ የሚቀርብ ጥያቄ ከስብሰባው አጀንዳ ጋር በማኅበሩ ጽ/ቤት በኩል ለማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡

13.9 የስብሰባው ቦታና ጊዜ

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ጥያቄው በቀረበ በሰባት ቀን ውስጥ የስብሰባውን ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳ በመግለጽ አግባብ ነው የሚለውን የማስታወቂያ ዘዴ በመጠቀም ስብሰባውን ይጠራል::

13.10 ምልዐተ ጉባዔ

ለጠቅላላ ጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ በአንቀጽ 9.6 የተጠቀሰውን ካሟሉ አባላት አምሳ በመቶ (50%) በላይ የተገኙ እንደሆነ ምልዐተ ጉባዔ እንደሞላ ይቆጠራል፡፡ ይህ ካልተሟላ በአንቀጽ 13.6.2 የተጠቀሰው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

13.11 አብላጫ ድምፅ

በአስቸኳይ ስብሰባ የሚወሰን ማናቸውም ውሣኔ በስብሰባው በተገኙት አባላት በሁለት ሦስተኛ ($^{2}/_{3}$ ኛ) ድምፅ መደገፍ ይኖርበታል።

አንቀጽ 14
ስለአዲተሩ ተግባርና ኃላፊነት

አዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

14.1 የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት አስተዳደር በሕግና በማኅበሩ መመሪያ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣ ጉድለቶች ቢኖሩ በጊዜው እንዲታረሙ ያደርጋል፣

14.2 የማኅበሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የልዩ ልዩ ኮሚቴዎችና የጽ/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ በሕግና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ፣ በወጡ ዓመታዊ ዕቅዶች መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣

14.3 የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ቃለ-ጉባዔዎች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

14.4 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፣

14.5 በዚህ አንቀጽ ለኦዲተሩ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ቢኖርም ማኅበሩ በማናቸውም ጊዜ በውጭ ኦዲተር ሂሣቡን ሊያስመረምር ይችላል።

አንቀጽ 15
ስለሥራ አስፈፃሚው ቦርድ

15.1 የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ሰባት (7) አባላት ይኖሩታል፣ እነርሱም:-

15.1.1 ፕሬዚዳንት፣

15.1.2 ምክትል ፕሬዚዳንት፣

15.1.3 ዋና ፀሐፊ፣

15.1.4 ሂሳብ ሹም፣

15.1.5 ሌሎች ሦስት (3) አባላት ናቸው::

15.2 የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት (3) ዓመት ይሆናል። አባላቱ በተከታታይ ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ለሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባልነት ሊመረጡ አይችሉም፤

15.3 በአንቀጽ 15(2) የተደነገገው ቢኖርም፣ የአመራር ተከታታይነትን ለማረጋገጥ በማንኛውም ምርጫ ወቅት ከነባር የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ውስጥ ሁለት አባላት (2) በአዲሱ ኮሚቴ ውስጥ እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 16
የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ ተግባር

16.1 የማኅበሩ ዓላማዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል።

16.2 የማኅበሩን ስትራተጂክ ፕላን፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል። ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ያፀድቃል። ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ያስፈጽማል፤

16.3 ለጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርቡ የሥራ ክንውንና ሌሎች ሪፖርቶችንና አጀንዳዎችን ያሻሽላል፣ ያፀድቃል፤

16.4 ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ የማኅበሩን ዋና ዋና የሥራ ዘርፍ ኃላፊዎችን ምደባና ስንብት ያፀድቃል፣

16.5 በማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት ለውጥ ላይ ይወስናል።

16.6 ገንዘብ መበደርን፤ ንብረት በዋስትና ማስያዝን፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት መግዛትና መሸጥን፣ ኢንቨስት ማድረግን፣ ስጦታ መስጠትን፣ ስምምነት መፈራረምን በተመለከተ ውሣኔ ይሰጣል፣

16.7 በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ተመሥርተው የሚወጡ መመሪያዎችን ያሻሽላል፣ ያፀድቃል፤

16.8 እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ክፍሎችን፣ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን፣ ያቋቁማል፣ ያሻሽላል፣አባላቱን ይሰይማል፤ ከቦርዱ በታች የሚገኘውን የማኅበሩን መዋቅር ያሻሽላል፣

16.9 በተለያየ ምክንያት በሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ አባልነት መቀጠል የማይችሉ አባላት ሲኖሩ ቀጣይ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ሌሎች አባላትን ተክቶ ይሰራል፤

16.10 ከማኅበሩ ጽ/ቤት በሚቀርቡለትና በሥልጣኑ ወሰን ክልል ውስጥ ባሉ ሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

16.11 የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራት ሁሉ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

16.12 ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤ እንዲሁም

16.13 ዋና ዳይሬክተሩ ከሌሎች የድርጅቱ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በጣምራ የማኅበሩን የባንክ ሂሣብ እንዲያንቀሳቅስ፣ የማኅበሩን ቼኮችና የገንዘብ ሰነዶች እንዲፈርም ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል።

አንቀጽ 17
የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ስብሰባ

17.1 የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ መደበኛ ስብሰባ የሚካሄደው በወር አንድ ጊዜ ይሆናል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜም ሊካሄድ ይችላል።

17.2 ከሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ አባላት ሃምሣ በመቶ (50%)+1 ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል።

17.3 የመደበኛ ስብሰባ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምጽ ይሆናል። ድምጽ እኩል በሆነ ጊዜ ፕሬዚዳንቱ ያለበት ወገን አብላጫ ድምጽ እንዳለው ይቆጠራል።

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 18
ስለፕሬዚዳንቱ ተግባርና ኃላፊነት

ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣ እነዚህንም ይህን ደንብና የማኅበሩን መመሪያዎች በመከተል ተግባራዊ ያደርጋል፣

18.1 የማኅበሩን ተግባራት እና እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣

18.2 የማኅበሩን ስትራተጂክ ፕላን፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፣ በጠቅላላ ጉባዔው ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

18.3 የጠቅላላ ጉባዔውንና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፤

18.4 በቋሚ ኮሚቴዎች አባልነት የሚሰየሙ ግለሰቦችን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በዕጩነት ያቀርባል፤

18.5 ውሎችን ይፈራረማል፣ በሕግ መሠረትና የማኅበሩን ገለልተኛነትና ነፃነት በማይነካ መልኩ ከልዩ ልዩ አካላት እርዳታ ይቀበላል፤

18.6 ማኅበሩን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤

18.7 የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ከሂሳብ ሹመ ወይም ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በጣምራ በመፈረም ያንቀሳቅሳል፤

18.8 ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲወስን በማኅበሩ ስም ከባንክ ይበደራል፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢና ሽያጭ ይፈፅማል፣ ካፒታል ኢንቨስት ያደርጋል፣ ስጦታ ይሰጣል፣ ማኅበሩን በመወከል ክስ ያቀርባል፣ ጠበቃ ይወክላል፤

18.9 በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 19
ስለምክትል ፕሬዚዳንቱ ተግባርና ኃላፊነት

ምክትል ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

19.1 ፕሬዚዳንቱ በሌለበት ጊዜ፣ ኃላፊነቱን ሲለቅ ወይም ሥራውን ለመሥራት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሠራል፣

19.2 ማኅበሩ ቋሚ ሠራተኛ ያልመደበ ከሆነ፣ የማኅበሩን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እንቅስቃሴና የሥራ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤ ስለአፈፃፀማቸው ለፕሬዚዳንቱና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

19.3 ሌሎች በሥራ አስፈፃሚ ቦርዱና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 20
ስለዋና ፀሐፊው ተግባርና ኃላፊነት

ዋና ፀሐፊው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

20.1 ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር የማኅበሩን የጽ/ቤት ሥራዎች ተግባራዊነት ይከታተላል፤

20.2 የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችና ውሳኔዎችን በቃለ-ጉባዔዎች መያዛቸውን ያረጋግጣል፡፡

20.3 የማኅበሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ቅጥር፣ አስተዳደርና ስንብት በሕግና በማኅበሩ መመሪያዎች መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፣

20.4 የማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ሥራ በሥርዓት መመራቱን ይከታተላል፤

20.5 ሌሎች በፕሬዚዳንቱና በሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 21
ስለሂሳብ ሹመ ተግባርና ኃላፊነት

የሂሳብ ሹመ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

21.1 የማኅበሩ ገንዘብ የማኅበሩ የውስጥ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት እየተንቀሳቀሰና እየተሠራበት መሆኑን ይከታተላል፤

21.2 የማኅበሩ ሂሳብ አያያዝና አስተዳደር በማኅበሩ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም በመደበኛ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤

21.3 የማኅበሩን ወጪዎች ከማኅበሩ ፕሬዚዳንትና ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በጣምራ ያፀድቃል፤

21.4 የማኅበሩ ንብረት በአግባቡ መመዝገቡንና መጠበቁን ያረጋግጣል፤

21.5 የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ ከፕሬዚዳንቱ ወይም ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣ እንዲሁም

21.6 ለሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ የሚቀርበውን የሦስት ወር ሂሳብ ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፡፡

አንቀጽ 22
ስለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት

22.1 የማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ፕሬዚዳንት ነው፡፡

22.2 ጽሕፈት ቤቱ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ይኖሩታል፡፡

22.3 ጽሕፈት ቤቱ በአንድ ተቀጣሪ ዋና ዳይሬክተር ይመራል፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 23
የስለዋና ዳይሬክተሩ ተግባርና ኃላፊነት

23.1 ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ፕሬዚዳንት ነው።

23.2 ዋና ዳይሬክተሩ፣ የማኅበሩን የቀን ተቀን እንቅስቃሴ ይመራል፣

23.3 ዋና ዳይሬክተሩ፣ የሥራ ዘርፎችን ያስተባብራል። የማኅበሩን ስትራቴጂክ ፕላን፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች፣ የውስጥ መመሪያዎች ያዘጋጃል። ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል። በተገቢው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

23.4 ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ ዋና ዋና የሥራ ዘርፍ ኃላፊዎችን ምደባ በተመለከተ ለሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

23.5 የማኅበሩ የሂሳብ አስተዳደር በማኅበሩ ደንብና በመደበኛ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት እንዲሆን ያደርጋል፤

23.6 ከፕሬዚዳንቱና ከዋና ፀሐፊው ጋር በመመካከር አጀንዳ ያዘጋጃል፤ የአጀንዳ ጉዳዮችን በማሰባሰብ ለሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ ስብሰባ ያቀርባል፣

23.7 የሥራ አስፈጻሚውን እና የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔዎች ከዋና ጸሐፊው ጋር በመመካከር ይይዛል፣ እንዲያዝ ያደርጋል፤

23.8 የማኅበሩን ገቢ ማዳበሪያ ሥልቶችን ይቀይሳል። ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

23.9 አባላትንና የማኅበሩን ሥራዎች የሚመለከቱ መረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ ያደርጋል፣

23.10 የሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ በሚወስነው የደሞዝና የአበል ስኬል መሠረት፣ ለእርሱ ተጠሪ ከሆኑ ዋና ዋና ሥራ መሪዎች በቀር፣ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

23.11 የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ ከፕሬዚዳንቱ ወይም ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል።

23.12 የማኅበሩን የሦስት ወርና ዓመታዊ የሂሳብና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር ለሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ ያቀርባል፣

23.13 ሌሎች በፕሬዚዳንቱ እና በዋና ፀሐፊው የሚሰጡትን ተግባራት ይፈፅማል፤

23.14 በአጠቃላይ ከሚመለከታቸው የማኅበሩ ሹሞች፣ ሌሎች ተመራጮችና ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን የማኅበሩ ሥራዎች በመተዳደሪያ ደንቡ፣ በየጊዜው በሚተላለፉ ውሳኔዎችና በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት እንዲፈፀሙ ተገቢውን ሁሉ ያደርጋል።

አንቀጽ 24
ስለማኅበሩ ቋሚ ኮሚቴዎች

24.1 ማኅበሩ የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፣

24.1.1 የሕግና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ፤

24.1.2 የአባላት እና የሕዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ኮሚቴ፤

24.1.3 የሕግ ጥናት፣ ሕትመትና እና ሥልጠና ኮሚቴ፤

24.1.4 የነፃ የሕግ አገልግሎት ኮሚቴ፤

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 25
ስለማኅበሩ ቋሚ ኮሚቴዎች አበላት አና ተጠሪነት

25.1 የእያንዳንዱ ኮሚቴ አባላት ብዛት ከ3 የማያንስ ከ5 የማይበልጥ ይሆናል፤

25.2 እያንዳንዱ ኮሚቴ የሚሰሠራበትን የውስጥ ደንብ፣ ፖሊሲና ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

25.3 ማኅበሩ ቋሚ ሠራተኛ ያልመደበ ከሆነ፣ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸው ለማኅበሩ ም/ፕሬዚዳንት ይሆናል፤ ስለሥራ አፈፃፀማቸው ለም/ፕሬዚዳንቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

አንቀጽ 26
ስለኮሚቴዎቹ ተግባርና ኃላፊነት

26.1. የሕግና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ፣

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

26.1.1. በሀገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብት ሁኔታ መርምሮ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፤

26.1.2. በሀገሪቱ የሚወጡ ሕጎች ሀገሪቱ ከፈረመቻቸው ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ከሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት ጋር ተጣጥመው የሚሄዱ መሆኑን ይመረምራል፣ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

26.1.3. የሕግ የበላይነትና የዳኝነት ነፃነት መከበሩንና የፍትሕ አስተዳደር በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚካሄድ መሆኑን ይከታተላል፤

26.1.4. ተገቢውን ጥናት በማድረግ ሕጎች እንዲሻሻሉ አዳዲሶችም እንዲወጡ አማራጭ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

26.1.5. ከሌሎች ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀት ለሕግ የበላይነት መከበርና ለሰብአዊ መብቶች መጠበቅ አጋዥ የሆኑ የግንዛቤ ማሳደጊያ ጽሑፎችና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

26.1.6. የኮሚቴውን የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፤

26.1.7. የሚሰጡትና ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

26.2 **የአባላትና የሕዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ኮሚቴ፣**

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

26.2.1 **ፍቃደኛ የሕግ ባለሙያዎች የማኅበሩ አባላት፣ የሕግ ተማሪዎች ተባባሪ አባላት እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል፤**

26.2.2 **ማኅበሩንና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ያስተዋውቃል፣ የማኅበሩን ዓላማዎች ለማሳካት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ከሚገኙ ድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር ግንኙነት የሚመሠረትበትንና የሚጠናከርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣**

26.2.3 **ከሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ጋር በመተባበር የማኅበሩን አባላት ጥናታዊ ጉዞዎች ያስተባብራል፣**

26.2.4 **አባላት እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች በሥነ ምግባር እና በሕግ እውቀት የላቀ ብቃት እንዲኖራቸው የሚረዱ ስልጠናዎች እና ሌሎች ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤**

26.2.5 **በፍርድ ቤቶች፣ በፍርድ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ ጥናት ያካሂዳል፤ ስለሚሻሻሉበት መንገድ ውይይት ያዘጋጃል፣ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡**

26.2.6 **በአባላት መካከል ወንድማማችነትና እህትማማችነት እንዲጠናከር፣ ሙያዊ መቀራረብ፣ ግንኙነትና ትብብር እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤**

26.2.7 **የማኅበሩ አባላት የሚገናኙበት፣ የሚወያዩበት፣ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚያገኙበት የሕግ ባለሙያዎች ክበብ እንዲቋቋምና እንዲጠናከር ያደርጋል፤**

26.2.8 **ከሚመለከታቸው ኮሚቴዎችና አካላት ጋር በመተባበር አባላት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የልምድ ልውውጥ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፤**

26.2.9 **ለአባላት ልዩ ልዩ የትምህርታዊ ጉብኝት ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ጥረት ያደርጋል፤ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤**

26.2.10 **የኮሚቴውን ስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፤**

26.2.11 **በሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡**

26.3 **የሕግ ጥናት፣ ሕትመትና እና ሥልጠና ኮሚቴ፤**

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

26.3.1 **ለምርምርና ጥናት የሚሆኑ ወቅታዊ ሕግ ነክ ርዕሶችን ይመርጣል፣ አባላት እና ሌሎች የሕግ ባለሞያዎች በሕግ ጥናትና ምርምር ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤ የምርምር ሥራዎቻቸውን የሚያቀርቡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣**

26.3.2 **ደረጃቸውን የጠበቁትና በኢዲቶሪያል ቦርዱ የተመረጡ በአባላቱ ጥናትና መርምር የተዘጋጁ ጽሑፎች እና ሌሎች ሕግ ነክ ጽሑፎችና ጥናቶች በማኅበሩ መጽሔት እንዲወጡ ያመቻቻል፣**

26.3.3 **የምርምር ጹሑፍ ለሚያዘጋጁ ግለሰቦች የሚከፈል አበል ይወስናል፤**

26.3.4 **ዕጩ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላትን ለሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤**

26.3.5 **የማኅበሩ ልዩ ልዩ የምርምር ሥራዎችና ጎትመቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤**

26.3.6 **ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የምርምር እና ጥናት ሥራ ግንኙነት እንዲመሠረት ይሠራል፤**

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

26.3.7 ለጎትመት ሥራ አጋዥ የሆኑ የገንዘብ ምንጮች የሚገኙባቸውን መንገዶች ይቀይሳል፤ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

26.3.8 ጎትመቶች የሚሸጡባቸውን ዋጋ በተመለከተ ለሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ ሀሳብ ያቀርባል፤

26.3.9 ለአባላቱ እና ለሌሎች የሕግ ባለሞያዎች በተለያዩ የሕግ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና እያዘጋጀ ይሰጣል፣

26.3.10 ማኅበሩ ለሚያዘጋጃቸው ሥልጠናዎች አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን ይመርጣል፣ የሚከፈላቸውንም አበል ይወስናል፤

26.3.11 የኮሚቴውን የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፣

26.3.12 በሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

26.4 **የነፃ የሕግ አገልግሎት ኮሚቴ፣**

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

26.4.1 አባላቱ እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች በነፃ የሕግ አገልግሎት ፕሮግራም አገልግሎት በመሥጠት ሥራ ላይ እንዲሣተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፤

26.4.2 የነፃ የሕግ አገልግሎት ማዕከላት እንዲቋቋሙ ጥናት ያካሂዳል፣ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ማዕከላቱን ያደራጃል፣ ይመራል፤

26.4.3 የማኅበሩ የነፃ የሕግ አገልግሎት ማዕከላት ተግባራቸውን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችላቸው የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

26.4.4 ነፃ የሕግ አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ማኅበራትና ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነትና የሥራ ቅንጅት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

26.4.5 ከሚመለከታቸው ኮሚቴዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለፕሮግራሙ ማጠናከሪያ የሚሆን የገንዘብ፣ የማቴሪያልና ሌላም ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

26.4.6 የነፃ የሕግ አገልግሎት ማዕከላትንና ሌሎች የኮሚቴውን እንቅስቃሴዎች እየገመገመ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

26.4.7 የኮሚቴውን ስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች ለማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፤

26.4.8 የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 27
የማኅበሩ የገንዘብ ምንጮች

የማኅበሩ የገንዘብ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፣

27.1 ከአባላት የሚሰበሰብ መዋጮ፣

27.2 የማኅበሩ ነፃነት ሳይነካና በሕግ መሠረት ከልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኙ ስጦታዎችና እርዳታዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የገንዘብ ማስገኛ ዝግጅቶች፣

27.3 የመጽሔትና የልዩ ልዩ ጎትመቶች ሽያጭ፣

27.4 ከሰልጣኞች የሚሰበሰቡ ገቢዎች::

27.5 ከሌሎች ሕጋዊ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች፣

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

አንቀጽ 28
ስለማኅበሩ የገንዘብ አያያዝ

28.1 ማንኛውም የማኅበሩ ገንዘብ በማኅበሩ ስም በባንክ ይቀመጣል፣

28.2 በሌላ ሁኔታ በሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ እስካልተወሰነ ድረስ፣ የማኅበሩ የባንክ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በፕሬዚዳንቱና በሂሳብ ሹሙ ወይም በዋና ዳይሬክተሩ ማለትም ከሦስቱ በሁለቱ ጣምራ ፊርማ ይሆናል።

አንቀጽ 29
ስለማኅበሩ የሂሳብ ዘመን

የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ይሆናል።

አንቀጽ 30
ደንቡን ስለማሻሻል

30.1 ይህን ደንብ የማሻሻል ሥልጣን የጠቅላላ ጉባዔው ነው፣

30.2 የማኅበሩ ደንብ የሚሻሻለው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9.6 የተጠቀሰውን አሟልተው በስብሰባው ከተገኙት አባላት በሁለት ሦስተኛ (2/3ኛ) ድምፅ ሲወሰን ነው።

አንቀጽ 31
ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ማኅበሩ ..... ቀን 2016 ዓ.ም ባደረገው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ፀደቀ። በፌደራል የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን ተረጋግጦ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሌላ ጠቅላላ ጉባዔ እስካልተሻሻለ ድረስ የፀና ይሆናል።

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT

መተዳደሪያ ደንቡ በተሻሻለበት ወቅት በጠቅላላ ጉባዔው ላይ የነበሩ የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

ተ.ቁ	ስም	አድራሻ	ክፍለ ከተማ	ቀበሌ	የቤት ቁ.	ስልክ ቁ.	ፊርማ
1							
2							
3							
4							
5							
6							
7							
8							
9							
10							
11							
12							

DANIEL FIKADU LAW OFFICE HTTPS://T.ME/LAWETHIOPIACOMMENT